የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
በያሉበት

ቁጥር/ Ref.No. 63/0130/14
ቀን/Date መጋቢት 1-4-2014

ለጉምሩክ ሥራ አመራር ስርዓት ፕሮጀክት ጽ/ቤት
ጉምሩክ ኮሚሽን

ጉዳዩ፡- የቆርኪና እና የምግብ ማሸጊያ አምራች ኢንዲስቱሪዎች በታሪፍ ቁጥር 7210.5090 የሚመደቡ እቃዎችን ለግብዓትነት ወደ አገር ሲያስገቡ ሱር ታክስ የማይመለከታቸው ስለመሆኑ፡፡

አንዳንድ የቆርኪና እና የምግብ ማሸጊያ አምራች ኢንዲስቱሪዎች በታሪፍ ቁጥር 7210.5090 ላይ የሚመደቡ እቃች ላይ ሱር ታክስ በገንዘብ ሚኒስቴር በተላለፈ ደብዳቤ መሰረት መክፈል የሌለባቸው ቢሆንም በአንዳንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሱር ታክስ እንዲከፍሉ እየተጠየቁ መሆኑን ጠቅሰዉ በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ጠይቀዋል፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ-30/7/1822 በ18/02/2014 በተጻፈ ደብዳቤ በታሪፍ ቁጥር 7210.5000 የሚመደቡ እቃዎችን የቆርኪ እና የምግብ ማሸጊያ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለግብዓትነት ሲያስመጧቸው በሚያቀርቡት የታደሰ የኢንቨስትመንት እና የንግድ ፈቃዳቸው መሰረት በዘርፉ የተሰማሩ መሆናቸው እየተረጋገጠ ከሱር ታክስ ነጻ እንዲሆኑ ወስኗል፡፡ ነገር ግን የታሪፍ ቁጥር 7210.5000 እ.ኤ.አ. ጥር 1/2022 ጀምሮ ተግባራዊ በተደረገው የታሪፍ ማሻሻያ በብሄራዊ ታሪፍ ቁጥር 7210.5010 (--ታተመ በሚል የጉምሩክ ቀረጥ 15%) እና 7210.5090 (---ሌሎች በሚል የጉምሩክ ቀረጥ 25%) ሆኖ ለሁለት የተከፈለ ስለሆነ የተጠቀሱት ኢንዱስትሪዎች በታሪፍ ቁጥር 7210.5090 የሚመደቡ እቃዎችን ወደ አገር ሲያስገቡ ሱር ታክስ እንደማይመለከታቸው ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የታሪፍ ቁጥር 7210.5000 በተጠቀሱት የኢንዱስትሪ ዘርፎች ለተሰማሩ አምራቾች ከሱር ታክስ ነጻ የተደረገ እስከሆነ ድረስ ታሪፍ ቁጥሩ በብሄራዊ ታሪፍ ለሁለት መከፈሉ በሱር ታክስ አከፋፈሉ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ አለመኖሩን በመገንዘብ በታሪፍ ቁጥር 7210.5090 የሚመደቡ እቃዎችን የቆርኪና እና የምግብ ማሸጊያ አምራች ኢንዲስቱሪዎች እ.ኤ.አ. ጥር 1/2022 ጀምሮ ለግብዓትነት ወደ አገር ሲያስገቡ በሚያቀርቡት የታደሰ የኢንቨስትመንት እና የንግድ ፈቃዳቸው መሰረት በዘርፉ የተሰማሩ መሆናቸው እየተረጋገጠ በተገቢው የጉምሩክ አሠራር ኮድ (CPC) መሰረት ከሱር ታክስ ነጻ ሆነው መስተናገድ ያለባቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር ከላይ የሰጠነውን ማብራሪያ እንዲያውቀው እና የተለየ አስተያየት ወይም ውሳኔ ካለው በአስቸኳይ እንዲያሳውቀን የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ ተደርጎለታል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ለገሰ አለማው
የታሪፍና ሥራት አገር አመሳስን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ፡-
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለታሪፍ ፖሊሲ ጥናትና ትንተና ቡድን
- ለታሪፍ ምደባ አሠራርና ድጋፍ ቡድን
  ጉምሩክ ኮሚሽን
- ለገንዘብ ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

CGF CROWN CORK MANUFACTURING PLC
ሲ.ጂ.ኤፍ፡ ቆርኪ. ማምረቻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ቁጥር፡ ሰጂኤፍ/ክራውን/0015/22
ቀን፡ ጥር 18 2014

**ለቀረጥ ተመላሽ ክፍል**
**ሞጆ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት**
**ሞጆ**

ጉዳዩ፡ **ሱር ታክስ ተመላሽ እንዲደረግልን ስለመጠየቅ፡፡**

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር **ማኢ30/7/1822** በቀን **18/02/2014** ዓ.ም ለጉምሩክ ኮሚሽን በፃፈው ደብዳቤ ለቆርኪ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለግብዓትነት የሚጠቀሙበት ጥሬ እቃ በታሪፍ ቁጥር 7210.5000 ለተመደቡት የሱር ታክስ እንዲነሳላቸው እና በ2 ቀናት ውስጥ ስራ ላይ እንዲውል መመሪያ ያስተላለፈ ሲሆን የጉምሩክ ኮሚሽንም የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ፅ/ቤቶች በደብዳቤ ቁጥር **6-3/0056/14** በቀን **ጥቅምት 20 2014** ዓ.ም ማሻሻያው ስራ ላይ እንዲውል የስራ መመሪያ አስተላልፏል፡፡

ሆኖም ግን የጉምሩክ ኮሚሽን አዲሱን የታሪፍ መደብ ስራ ላይ ሲያውል ቀድሞ የነበረው የታሪፍ መደብ **7210 5000**ን ወደ **7210 5090** ሲቀይረው የሱር ታክሱን መልሶ በጉምሩክ ማስከፈያ ምጣኔ ውስጥ በስህተት ሲስተም ውስጥ አካቶታል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኩባንያችን **በገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋይ ቅ/ፅ/ቤት** ስር በግብር መለያ ቁጥር **0058681420** ተመዝግበን ተገቢውን ግብር እየከፈለን የምንገኝ ሲሆን ከዚህ በታች በተጠቀሰው የጉምሩክ ሰነድ ቁጥር **4-000287** በቀን **04/01/2022** ብር **1,264,628.00 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ስድሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ)** በጉምሩክ ሲስተም ላይ በጊዜው የሱር ታክስ በስህተት በመካተቱ ክፍያ ፈፅመናል፡፡

በመሆኑም ይህ በስህተት ሲስተም ላይ በመካተቱ በሱር ታክስ መልክ የከፈልነውን ብር **1,264,628.00 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ስድሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ)** ተመላሽ እንዲደረግልን እየጠየቅን ይህንኑ ጉዳይ እንዲያስፈፅሙ የኩባንያችን ባልደረባ የሆኑትን አቶ አብራሃም ሙሉጌታን የወከልን መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

ለሚደረግልን የዘውትር የስራ ትብብር በቅድሚያ እናመሠግናለን፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

Teibe G/Egziabher
General Manager

ኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ሰነዶች ክፍል ቁ.1
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

ቁጥር፡ ሲጂኤፍ/ክራውን/0014/22

ቀን፡ ጥር 18 2014

**ለቀረጥ ተመላሽ ክፍል**
**ሞጆ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት**
**ሞጆ**

ጉዳዩ: **ሱር ታክስ ተመላሽ እንዲደረግልን ስለመጠየቅ::**

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር **ማኢ30/7/1822** በቀን **18/02/2014** ዓ.ም ለጉምሩክ ኮሚሽን በፃፈው ደብዳቤ ለቆርኪ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለግብዓትነት የሚጠቀሙበት ጥሬ እቃ በታሪፍ ቁጥር 7210.5000 ለተመደቡት የሱር ታክስ እንዲነሳላቸው እና በ2 ቀናት ውስጥ ስራ ላይ እንዲውል መመሪያ ያስተላለፈ ሲሆን የጉምሩክ ኮሚሽንም የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ፅ/ቤቶች በደብዳቤ ቁጥር **6-3/0056/14** በቀን **ጥቅምት 20 2014** ዓ.ም ማሻሻያው ስራ ላይ እንዲውል የስራ መመሪያ አስተላልፏል።

ሆኖም ግን የጉምሩክ ኮሚሽን አዲሱን የታሪፍ መደብ ስራ ላይ ሲያውል ቀድሞ የነበረው የታሪፍ መደብ **7210 5000**ን ወደ **7210 5090** ሲቀይረው የሱር ታክሱን መልሶ በጉምሩክ ማስከፈያ ምጣኔ ውስጥ በስህተት ሲስተም ውስጥ አካቶታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኩባንያችን **በገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋይ ቅ/ፅ/ቤት** ስር በግብር መለያ ቁጥር **0058681420** ተመዝግበን ተገቢውን ግብር እየከፈለን የምንገኝ ሲሆን ከዚህ በታች በተጠቀሰው የጉምሩክ ሰነድ ቁጥር **4-000304** በቀን **04/01/2022** ብር **640,522.00 (ስድሰት መቶ አርባ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሁለት)** በጉምሩክ ሲስተም ላይ በጊዜው የሱር ታክስ በስህተት በመካተቱ ክፍያ ፈፅመናል።

በመሆኑም ይህ በስህተት ሲስተም ላይ በመካተቱ በሱር ታክስ መልክ የከፈልነውን ብር **640,522.00 (ስድሰት መቶ አርባ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሁለት)** ተመላሽ እንዲደረግልን እየጠየቅን ይህንኑ ጉዳይ እንዲያስፈፅሙ የኩባንያችን ባልደረባ የሆኑትን አቶ አብራሃም ሙሉጌታን የወከልን መሆናችንን እንገልፃለን።

ለሚደረግልን የዘውትር የስራ ትብብር በቅድሚያ እናመሠግናለን።

"ከሠላምታ ጋር"

Teibe GEgziabher
General Manager

ቁጥር፡ ሲጂኤፍ/ክራውን/0013/22
ቀን፡ ጥር 18 2014

**ለቀረጥ ተመላሽ ክፍል**
**ሞጆ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት**
**ሞጆ**

ጉዳዩ: **ሱር ታክስ ተመላሽ እንዲደረግልን ስለመጠየቅ::**

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር **ማኢ30/7/1822** በቀን **18/02/2014** ዓ.ም ለጉምሩክ ኮሚሽን በፃፈው ደብዳቤ ለቆርኪ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለግብዓትነት የሚጠቀሙበት ጥሬ እቃ በታሪፍ ቁጥር 7210.5000 ለተመደቡት የሱር ታክስ እንዲነሳላቸው እና በ2 ቀናት ውስጥ ስራ ላይ እንዲውል መመሪያ ያስተላለፈ ሲሆን የጉምሩክ ኮሚሽንም የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ፅ/ቤቶች በደብዳቤ ቁጥር **6-3/0056/14** በቀን **ጥቅምት 20 2014** ዓ.ም ማሻሻያው ስራ ላይ እንዲውል የስራ መመሪያ አስተላልፏል።

ሆኖም ግን የጉምሩክ ኮሚሽን አዲሱን የታሪፍ መደብ ስራ ላይ ሲያውል ቀድሞ የነበረው የታሪፍ መደብ **7210 5000**ን ወደ **7210 5090** ሲቀይረው የሱር ታክሱን መልሶ በጉምሩክ ማስከፈያ ምጣኔ ውስጥ በስህተት ሲስተም ውስጥ አካቶታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኩባንያችን **በገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋይ ቅ/ፅ/ቤት** ስር በግብር መለያ ቁጥር **0058681420** ተመዝግበን ተገቢውን ግብር እየከፈለን የምንገኝ ሲሆን ከዚህ በታች በተጠቀሰው የጉምሩክ ሰነድ ቁጥር **4-000295** በቀን **04/01/2022** ብር **963,814.10 (ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ አራት ከ10/100)** በጉምሩክ ሲስተም ላይ በጊዜው የሱር ታክስ በስህተት በመካተቱ ክፍያ ፈፅመናል።

በመሆኑም ይህ በስህተት ሲስተም ላይ በመካተቱ በሱር ታክስ መልክ የከፈልነውን ብር **963,814.10 (ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ አራት ከ10/100)** ተመላሽ እንዲደረግልን እየጠየቅን ይህንኑ ጉዳይ እንዲያስፈፅሙ የኩባንያችን ባልደረባ የሆኑትን አቶ አብራሃም ሙሉጌታን የወከልን መሆናችንን እንገልፃለን።

ለሚደረግልን የዘውትር የስራ ትብብር በቅድሚያ እናመሠግናለን።

"ከሠላምታ ጋር"

Teibe G/Egziabher
General Manager

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION


ቁጥር/ Ref.No. 6.3/0056/14

ቀን/Date ጥቅምት 20 2014

የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
ባያሉበት

ለጉምሩክ ሥራ አመራር ሥርዓት ፕሮጀክት ጽ/ቤት
ጉምሩክ ኮሚሽን

ጉዳዩ፡- የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያን ይመለከታል

ከገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ሚአ.30/7/1822 በቀን 18/02/2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በየጊዜው በሚኖረው የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት አምራች ኢንዱስትሪዎች ለምርት ግብዓትነት በሚጠቀሚቸው ምርቶች ላይ የታሪፍ ማሻሻያ በማድረግ፤ እንዲሁም በታሪፍ ቁጥር 7210.5000 የሚመደቡ ዕቃዎች የቆርኪ እና የምግብ ማሸጊያ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሲያስመጧቸው ኢንቨስትመንትና ንግድ ፈቃዳቸው እየተረጋገጠ ከሱር ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ተወስኗል።

በዚሁ መሰረት አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነ ስርዓት በመፈፀም የታሪፍ ማሻሻያው በጉምሩክ መረጃ ቋት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ተቀባይነት ባገኙ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን እያሳሰብን ለአፈፃፀም ይረዳችሁ ዘንድ የማሻሻያውን ቅጂ ሁለት (02) ገፅ በተቋሙ መረጃ ስርዓት (Local Share ቁጥር \\10.12.0.8/Tariff Classification & Origin/Tariff Classification/ የታሪፍ ማሻሻያዎች) ሳጥን ውስጥ በታሪፍ ቁጥር 1507.9090፣ 1511.9090፣ 3402.1100፣ 3402.1200፣ 3402.1900፣ 7408.1100፣ 7408.1900፣ 7605.2100 እና 7605.2900 ላይ የተደረገ የታሪፍ ምጣኔ እና የሱር ታክስ ማሻሻያ" በሚል ስም የተቀመጠ መሆኑን እየገለፅን የጉምሩክ ሥራ አመራር ሥርዓት ፕሮጀክት ጽ/ቤትም አባሪ በተደረገው የታሪፍ ሠንጠረዥ መሰረት አስፈላጊውን የመረጃ ቋት ማስተካከያ እንዲያደርግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ካሣዬ አየለ ሞላ
የታሪፍ ምደባና ስሪት አገር አወሳሰን
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተወካይ

ግልባጭ፡-
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባ ፖሊሲ ጥናትና ትንተና ቡድን
- ለታሪፍ ምደባ አሰራርና ድጋፍ ቡድን
  የጉምሩክ ኮሚሽን
- ለኢትዮጵያ ጉምሩክ አስተላላፊዎች የሙያ ማህበር
- ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
  አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቤት
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
# MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር ሀ9/ኢ 30/7/1822
Ref. No
ቀን 18/2/2014
Date.

ለጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያን ይመለከታል፤

እንደሚታወቀው የ2017 የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ ከመስከረም 01 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ሲሆን፣ በዚህም ለረጅም ዓመታት ሲከማቹ የቆዩ በተለይም በአምራች ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ማነቆ የነበሩ ችግሮች ሊፈታ መቻሉ ከአምራች ኢንዱስትሪው እየቀረበ ያለው አስተያየት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሆኖ፤ በአንዳንዱ ንዑስ አንዳንድ ግብዓቶች ከመጨረሻ ምርቱ አንፃር ሲታይ ያላቸው የታሪፍ መጣኔ ተመሳሳይ በመሆናቸው፣ በዚህም የአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከውጪ ከሚገቡ ተመሳሳይ ምርቶች ጋር በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ከለላ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በዚህም፡

1. የሚከተሉት ታሪፍ ቁጥሮች የጉምሩክ ታሪፍ መጣኔያቸው እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

| ተቁ | የታሪፍ ቁጥር | የጉምሩክ ቀረጥ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | 1507.9090 | 5% |
| 2 | 1511.9090 | 5% |
| 3 | 3402.1100 | 5% |
| 4 | 3402.1200 | 5% |
| 5 | 3402.1300 | 5% |
| 6 | 7408.1100 | 5% |
| 7 | 7408.1900 | 15% |
| 8 | 7605.2100 | 5% |
| 9 | 7605.2900 | 15% |

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር
Ref. No ______________

ቀን
Date ______________

2. በታሪፍ ቁጥር 7210.5000 የሚመደቡ የቆርኪ እና የምግብ ማሸጊያ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለማበረታታት ሲያስመጧቸው የሚያቀርቡት የታደሰ የኢንቨስትመንት እና የንግድ ፈቃዳቸው እየተረጋገጠ ከሱር ታክስ ነፃ እንዲሆን ተወስኗል። አፈጻጸሙን በሚመለከት ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን በኋላ በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ ተቀባይነት በሚያገኝ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ላይ ተግባራዊ እንዲደረግ ተወስኗል።

ከሠላምታ ጋር

__ግልባጭ፡-__

- ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
  __አዲስ አበባ__
- ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
  __ገንዘብ ሚኒስቴር__

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1